የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

## በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ

(ከመስከረም 7- 14/2017 ዓ.ም)
(17 September- 24 September, 2024)

### 1.ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት በምንዛሪ ለውጡ የሚደርስበትን ኪሳራ የሚያካክስ የካፒታል ማሳደጊያ ሊደረግለት ነው

**Reporter: September 22, 2024**

- **በልዩ ሁኔታ ለነዳጅ ግዥ 670 ሚሊዮን ዶላር ተለቆለታል**

ተግባራዊ የሆነው ገበያ መር የውጭ ምንዛሪ ግብይት ሥርዓት በኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ላይ የሚያደርሰውን ኪሳራና ድርጅቱ ያሉበትን የንግድ ብድር ዕዳዎች ታሳቢ በማድረግ፣ መንግሥት የድርጅቱን ካፒታል ለማሳደግ መወሰኑ ተሰማ፡፡

በጉዳዩ ላይ ሪፖርተር መረጃ የጠየቃቸው የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ከፍተኛ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ዓለማየሁ ፀጋዬ፣ ‹‹መንግሥት የድርጅቱን ካፒታል ለማሳደግ ቃል ገብቷል፤›› ሲሉ አረጋግጠዋል።

https://www.ethiopianreporter.com/133623/

### 2. ከ30 ዓመት በላይ ያገለገሉ ድንበር ተሻጋሪ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት እንዳይሰጡ መወሰኑ ቅሬታ አስነሳ

**Reporter : September 22, 2024**

የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር አማራጭ መፍትሔ ሳያዘጋጅና በቂ ጥናት ሳያካሂድ፣ ‹‹ከ30 ዓመት በላይ አገልግሎት የሰጡ ድንበር ተሻጋሪ ተሽከርካሪዎች፣ አገልግሎት እንዳይሰጡ›› ብሎ ውሳኔ ማስተላለፉ፣ አግባብነት የሌለውና ከትራንስፖርት ዘርፍ የሚገኘውን ኢኮኖሚዊ ጥቅም የሚያሳጣ ነው ሲሉ በዘርፉ የተሰማሩ ቅሬታቸውን አቀረቡ፡፡

ቅሬታ አቅራቢዎቹ ቅሬታቸውን ያሰሙት ዓርብ መስከረም 10 ቀን 2017 ዓ.ም.፣ የኢትዮጵያ ትራንስፖርት አሠሪዎች ፌዴሬሽን በዘርፉ ከተሰማሩ ባለድርሻዎች ጋር ውይይት ባካሄደበት ወቅት ነው፡፡

የኅብረት ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር መሥራችና ዋና ዳይሬክተር አቶ ባይሳ አየለ ለሪፖርተር እንደገለጹት፣ የትንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ግልጽ የሆነ መመርያ ሳያወጣ፣ ለዓመታት አገልግሎት የሰጡ ድንበር ተሻጋሪ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት እንዳይሰጡ ማለቱ አግባብነት የለውም፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/133614/

### 3. ኢትዮ ቴሌኮም በሁሉም ደንበኞችና አገልግሎቶች ላይ ዋጋ እንደማይጨምር አስታወቀ

**Reporter:September 22, 2024**

መንግሥት በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የውጭ ምንዛሪ ተመን ገበያ መር ካደረገ በኋላ፣ በሁሉም ደንበኞችና አገልግሎቶች ላይ የዋጋ ጭማሪ እንደማያደርግ ኢትዮ ቴሌኮም አስታወቀ፡፡

ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ እንደተናገሩት፣ የውጭ ምንዛሪ ተመኑን ታሳቢ በማድረግ ሁሉም ደንበኞችና አገልግቶች ላይ ጭማሪ እንደማይደረግ፣ ነገር ግን የደንበኞችን የመክፈል አቅም በማገናዘብ በአንዳንድ አገልግሎቶችና በዝቅተኛ ተከፋዮች (የመግዛት አቅም በሌላቸው) ላይ ምንም ጭማሪ አይደረግም፡፡

ኢትዮ ቴሌኮም ያለበትን ወጪ በሚገባ በማስተዳደር፣ ወጪ ቆጣቢ የሆነ አሠራር በመከተልና የደንበኞችን የመክፈል አቅም ታሳቢ በማድረግ መጠነኛ የዋጋ ማሻሻያ እንደሚያደርግ ሥራ አስፈጻሚዋ አስረድተዋል፡፡

በ2017 በጀት ዓመት ኢትዮ ቴሌኮም የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ለማሳደግ ዕቅድ መያዙን፣ ለዚህም ዓለም አቀፍ ስትራቴጂካዊ አጋርነትን ለማስፋትና ተወዳዳሪ አገልግሎት በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ ሥራዎች ያከናውናል ብለዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/133604/

### 4. በመንግሥት ዋጋ ጭማሪ ሳቢያ ሰሊጥ በዓለም ገበያ ገዥ እያጣ ነው ተባለ

**Reporter:September 18, 2024**

መንግሥት ዋጋ ከፍ አድርጎ በመተመኑ የኢትዮጵያ ሰሊጥ በዓለም የገበያ ገዥ ማጣቱን፣ የጥራጥሬና ቅባት እህል ላኪዎች ተናገሩ፡፡

ከዓለም ገበያ ትልቁ መሆኑ በሚነገርለት የቻይና ገበያ ኢትዮጵያ ከነበራት 50 በመቶ ድርሻ ወደ አምስት በመቶ ዝቅ ማለቱን የወጡ ሪፖርቶች ያመለክታሉ፡፡

ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ የጥራጥሬና የቅባት እህል ላኪ ለሪፖርተር እንደተናገሩት፣ ታንዛኒያ፣ ቶጎና የሌሎች አገሮች ሰሊጥ በቶን እስከ 1,400 ዶላር ሲሸጡ፣ የኢትዮጵያ ግን 1,800 ዶላር በቶን ተመን ወጥቶለት ለገበያ ይቀርባል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/133570/

### 6. በመስከረም ወር የሚከበሩ በዓላት ላይ ለመሳተፍ የሚመጡ የውጭ ሀገራት ጎብኚዎች የቆይታ ጊዜን ለማራዘም ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል

**ኢ.ዜ.አ፡ መስከረም 11/2017**

በመስከረም ወር የሚከበሩ በዓላት ላይ ለመሳተፍ የሚመጡ የውጭ ሀገራት ጎብኚዎች የቆይታ ጊዜን ለማራዘም የቅድመ ዝግጅት ስራ መጠናቀቁን የቱሪዝም ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ ስለሺ ግርማ ለኢዜአ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች የበለጸገች ቢሆንም በቂ የቱሪዝም መሰረተ ልማት ባለመኖሩ ከዘርፉ የሚገባትን ጥቅም ሳታገኝ ቆይታለች፡፡

በተያዘው የ2017 በጀት ዓመት ከአንድ ሚሊየን በላይ የውጭ ጎብኚዎችን ለመሳብ እቅድ መያዙን ገልጸው፤ ለመዝናናት፣ ለኮንፍረንስ፣ ለኤግዚቢሽንና ሌሎች ዓላማዎች የሚመጡ እንግዶችን ቆይታ ለማራዘም የተለያዩ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5178857

### 7. የወጪ ንግዱን ከኪሳራ እንደሚታደግ የሚጠበቀው ማሻሻያ

**Ethiopian press:September 18, 2024**

መንግሥት በቅርቡ ወደ ትግበራ ያስገባው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሀገሪቷ በተለያዩ መስኮች የተረጋጋ የኢኮኖሚ ዕድገት እንድታስመዘግብ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል የሚል እምነት ተጥሎበታል። የዘርፎችን ምርታማነት ለማሳደግ እንዲሁም የማክሮ ኢኮኖሚ ችግሮችን ለመፍታት እንደሚያስችልም የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ይናገራሉ።

አካታችና ዘላቂ ዕድገት ያለው ኢኮኖሚን ለመገንባት፣ ሀገራዊ ገቢን ለማሳደግ የሚኖረው አበርክቶም ጉልህ ስለመሆኑም ተነግሮለታል። የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ተግባራዊ ካደረጋቸው ጉዳዮች መካከል የውጭ ምንዛሬ ግብይቱ ከብሔራዊ ባንክ እጅ ወጥቶ በገበያ የሚመራበት ሥርዓት መፈጠሩ አንዱ ሲሆን፤ ይህም በተለይ የወጪ ንግዱን ለማሳለጥ፣ በችርቻሮና ጅምላ ንግድ የውጭ ባለሀብቶችን ወደ ሀገር ውስጥ በመሳብ ሰፊ የንግድ እንቅስቃሴ እንዲፈጠር ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል።

https://press.et/?p=136714

### 8. ክላውድ ኮምፒውቲንግ- ዘመነኛው የመረጃ አያያዝ ዘይቤ

**Ethiopian press: September 17, 2024**

መረጃዎችን በማቆየት ወይም በማከመቻት በኩል ስልኮች፣ ኮምፒውተሮች፣ ፍላሾችና የመሳሰሉት ሀርድ ዲስኮች ሚና ከፍተኛ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ተቋማት፣ ግለሰቦች፣ ወዘተ. መረጃዎችን በማዕከላዊ የመረጃ ቋትነት /central database/ በሚገለገሉባቸው ኮምፒዩተሮች እያስቀመጡ ሲጠቀሙ ኖረዋል፤ ግለሰቦችም እንዲሁ በስልካቸው ወይም በላፕቶፖቻቸው አልያም በሲዲ እና ፍላሽን በመሳሰሉ ሀርድ ዲስኮች እያስቀመጡ ሲጠቀሙ ቆይተዋል፡፡ አሁንም ይህንኑ የሚያደርጉባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ሰርቨሮችን ሌሎች መረጃ የማከማቻ ቴክኖሎጂዎች ሆነው ቆይተዋል፡፡

ቴክኖሎጂ የወለደው መረጃ /Data/ የሚቀመጥበት አዲስ ዘዴ ክላውድ ቴክኖሎጂ ይሰኛል፡፡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ክላውድ ኮምፒውቲንግ ቴክኖሎጂ በፈረንጆቹ 1960ዎቹ ነው የተፈጠረው፡፡ ከዚያን ጊዜ አንስቶም ቴክኖሎጂውን መጠቀም የተጀመረ ሲሆን፣ እአአ በ2006 ደግሞ የአሜሪካው የቴክኖሎጂ ኩባንያ አማዞን የራሱን የክላውድ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል። ከዚያን ጊዜ አንስቶ አገልግሎት እየተስፋፋ መጥቶ ቀስ በቀስም ታዋቂነትን አግኝቶ የዲጂታል ቴክኖሎጂው የመረጃ አቀማመጥ ዘዴን መለወጥ ያስቻለ ቴክኖሎጂ ለመሆን በቅቷል፡፡

ተቋማትም ሆኑ ግለሰቦች በርካታ መረጃዎችን ረዘም ላሉ ጊዜያት ዲጂታል በሆነ መንገድ ማስቀመጥና መገልገል የሚችሉበት ብቻም አይደለም፤ መረጃው በአጋጣሚ ከግል ኮምፒውተሮቻቸው ውስጥ ቢሰረዝ ወይም የተቀመጠበት የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ ቢጠፋ እንኳን በሌላ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ ከክላውድ ላይ በማግኘትም መጠቀም ይችላሉ፡፡

ስልክ ብንቀይር እንኳን በቀድሞ ስልካችን ፎቶዎች፣ ቪዲዮዎች፣ የጽሑፍ መልዕክቶች እና የስልክ ቁጥሮችን የመሳሰሉ ጠቃሚ መረጃዎቻችን ወደ አዲሱ ስልካችን እንዲሸጋገር ለማድረግ እንደሚጠቅምም የዘርፉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ።

5. **ኢትዮጵያ የቁም እንስሳት ወጪ ንግድ ለመጀመሪያ ጊዜ በባቡር ወደ ጅቡቲ ማጓጓዝ ጀመረች**

**ኢ.ዜ.አ፡ መስከረም 13/2017**

ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የቁም እንስሳት ወጪ ንግድ በባቡር ከአዳማ ወደ ጁቡቲ ማጓጓዝ መጀመሯን የኢትዮ-ጁቡቲ የባቡር አክሲዮን ማህበር ዋና ስራ አስፈጻሚ ኢንጂነር ታከለ ኡማ ገለጹ።

ኢንጂነር ታከለ የተጀመረው ስራ ከዚህ ቀደም ለገቢ ምርቶች ብቻ ይውሉ የነበሩ የባቡር ፉርጎዎች በስፋት ለመጠቀም እንደሚያግዝ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት ገልጸዋል።

በተጨማሪም በእንስሳት ላይ የሚደርስን ጫና በመቀነስ የስጋ ምርት ጥራትን እንደሚያሳድግ ጠቅሰው ይህም ኢትዮጵያ ለዘላቂና ውጤታማ ንግድ ያላትን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ድንበር ተሻጋሪ የካፒታል ፍሰት እንዲያድግ አበክራ እየሰራች መሆኑንም ጨምረው ጠቁመዋል።

**https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5186265**

## *በውጭ ቋንቋዎችና ከውጭ ሚዲያዎች*

**9. Ethio telecom keen on USD 1bln expansion project**

**Reporter: September 21, 2024**

Ethio telecom is on the hunt for financing to back plans for massive infrastructure expansions over the fiscal year, with the state-owned giant's executive team looking to spend up to USD one billion on the ambitious project.

The telecom operator envisions a 75 percent growth in revenues in 2024/25, as Frehiwot and her team target bringing in close to 164 billion birr, including USD 283 million in foreign currency from international service provision. A cost optimization program is envisioned to trim up to 3.2 billion birr from company expenditures.

**https://www.thereporterethiopia.com/41992/**

**10. MINTEX Mining, Technology Expo to Be Held in Addis Ababa**

**ENA: September 24/2024**

The third MINTEX Mining and Technology Expo will be held in Addis Ababa at the Millennium Hall on November 23-26, 2024, Ethiopia's Ministry of Mines announced.

Several international companies engaged in the sector are expected to participate at the four day event.

The Expo is expected to highlight Ethiopia's mining potential and encourage investment in the industry by drawing technology providers and mining investors together.

The event also plays pivotal role in terms of promoting the products of Ethiopian investors engaged in the sector to the international market.

The ministry said the necessary preparations have been completed to conduct the expo successfully.

The ministry said the necessary preparations have been completed to conduct the expo successfully.

Ethiopia is endowed with vast mineral resources including gold and precious stones that hold immense potential to transform the country's economy.

**https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5189358**

**10.** Ethiopia's Growing Economy, Strategic Position in Africa Opens Doors for Deepened BRICS Collaboration

**ENA: September 22/2024**

Ethiopia's growing economic and strategic position in Africa can

**11. Kenya's power imports from Ethiopia up in six- month**

**Ethiopian press: September 24, 2024**

Kenya's electricity imports from Ethiopia rose 88 percent in the first six months of 2024 as compared to a similar period in 2023, as the East African nation sought cheaper hydropower, the national statistics bureau said in a report Friday.

Kenya National Bureau of Statistics (KNBS) said the country imported 672.26 million kilowatt-hours (kWh) of power from Ethiopia during the six months, an increase from 357.44 million kWh a year ago.

The imports have been on the rise, growing from a low of 20 million kWh a month in 2023 to a high of 122 million kWh per month in 2024.

According to KNBS, supply from Ethiopia makes the bulk of the power imports for Kenya, with imports from Uganda registering a decline to 106.07 million kWh in the six months, from 141.23 million kWh in a similar period in 2023.

**https://press.et/herald/?p=102794**

**12.Nation Ready to Welcome Tourists for Upcoming Festivals in Ethiopia: Tourism Ministry**

**ENA:September 24/2024**

Ethiopia as always is ready to welcome tourists who will attend the various upcoming cultural and religious festivals celebrated in the country, Ministry of Tourism revealed.

State Minister of Tourism, Sileshi Girma told ENA that massive preparations are underway aimed at creating an enabling environment for tourists who are going to visit Ethiopia to attend the cultural and religious festivals as well as the tourism sites of the country.

Ethiopia celebrates various cultural and spiritual festivals including the UNESCO prescribed ones starting from the month of September.

Meskel (Founding of True Cross), Irrecha (Thanks giving festival) and Timket (Epiphany) are among the major outdoor festivals celebrated in the country colorfully.

**https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5191064**

**13.Ethiopia Participates At FAO's Global Conference on Animal Health in Rome**

**ENA: September 23/2024**

The Food and Agriculture Organization of the United Nations (FAO) today opened its first-ever Global Conference on Animal Health Innovation, Reference Centres and Vaccines, aimed at tackling animal diseases.

Ethiopia has been represented by Girma Amente, Minister of Agriculture, according to Ethiopian Embassy in Rome.

In his speech during the opening session, the minister stressed the importance of animal health and innovation and preventive vaccines production and distribution to other African countries.

He appreciated FAO, WHO and UNICEF for their unreserved support for the protection and eradication of transboundary pandemic diseases and strengthening one health approach.